# ወንጌልን የማዳረስ አገልግሎትና ሥነ ጽሁፍ (ክፍል - 2)

(በፍሬው አድነው)

ወንጌልን የማዳረስ ስራ ዳግም የተወለደ ክርስቲያን ተልእኮና የእምነቱ መሰረት እንደሆነ በመግለጽ፣ ለዚህ ማሳያ እንዲሆነኝ አራት የወንጌል መልእክት አቀራረቦችን በመምረጥ ከማቀርበው ተከታታይ ጽሁፍ ውስጥ ይህ ሁለተኛው ክፍል ነው፡፡ ቀደም ሲል እንብበን፣ ዙሪያ ገባውን እያየን የእግዚአብሔር ስም የሚከብርበትን መንገድና ወንጌል የበለጠ የሚስፋፋበትን ስልት ከዚያ ነቅሰን ብንማማር ደስ እንደሚለኝም ገልጬ ነበር፡፡

ይሁን እንጂ፣ ሁሉንም በመዘርዘር የሌሎች ጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉ አስተያየቶችን እንዳላመክን በማሰብ ከዚህ የሚቀጥሉትን ሁለት ክፍሎች ለጊዜው ገታ ማድረጉን መረጥኩ፡፡ ስለዚህ በቀጣዮቹ ሁለት ርዕሶች ዙሪያ ያለኝን እስክሰነዝር በቀረቡት ሁለቱ ላይ አንባቢያን እንዲወያዩና ያላቸውን ሀሳብ በመስጠት እንዲሳተፉ ጥሪዬን አቀርባለሁ፡፡ የዛሬው ርዕስ **"ለየት ያለ የዝማሬ አገልግሎት - ሰዎችን በቋንቋቸው መድረስ"** የሚል ነው፡፡ በጽሁፉ ማብቂያ ላያይዘው ያሰብኩትን፣ የተጠቀምኩባቸውን ጥቀት የማጣቀሻ መረጃዎች ዝርዝርም ማግኘት ይቻላል፡፡

## 2. <u>ለየት ያለ የዝማሬ አገልግሎት - ሰዎችን በቋንቋቸው መድረስ</u>

ለባህል ለውጦች ምክንያት የሚሆኑ ግፊቶች በተለያዩ ምክንያቶች ይከሰታሉ፡፡ በተለይ በአሁኑ ጊዜ በዓለም አቀፍ ደረጃ "ግሎባላይዜሽን" በሚባለው መርህም ሆነ "በወዳጅነት" ሰበብ 'ተጽእኖ የሚያደርገው አካል' ባህል በሚደረግበት ላይ የራሱን ማራገፉና የነበረውን መጫኑ አይቀሬ ነው፡፡ ለዚህ እንደ ምሳሌ፣ የበለጸጉ የሚባሉት ሀገሮች በማደግ ላይ ያሉ ሀገሮች ባህሎች ላይ የሚያሳድሩት የጎላ ተጽእኖ ስለመኖሩ የሚያመለክቱ ብዙ ጥናቶችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ መንገዱ በመገናኛ ብዙሃኑ፣ በኪነ ጥበቡ፣ በትራንስፖርቱ፣ በሃይማኖቱ፣ በስነ ጽሁፉም ሆነ በምን ይባል ብቻ ለውጦቹ አዎንታዊና አሉታዊ ተጽእኖ ማሳደራቸውን መካድ አይቻልም፡፡

በወንጌል ስርጭት የመጀመሪያዎቹ ዓመታት በኢትዮጵያ የሆነውም እንደዚያ ነው፡፡ እዚህ የምንወያየው ወንጌልን በተመለከተ ስለሆነ ቀደም ብሎ ከነበረው "ባህላዊ እምነት" ወይም "ልማድ" አኳያ በክርስትና የመተካቱን ለውጥ በአዎንታዊነቱ እምንደግፈው ሊሆን ይችላል፡፡ አቀራረቡና አፈጻጸሙን በተመለከተ ግን በመረዳትና በመከባበር ሳይሆን አንዳንዴም የነበረውን ባህላዊ መሰረት ሁሉ በመናድ ላይ ያተኮረ ስለነበረ ጠባሳ ትቶ ማለፉን መካድ አይቻልም፡፡ በምሳሌ ሀሳቤን ማስጨበጥ ብችል ኋላ ላይ የማነሳውን ወቅታዊ ማሳያ ለማያያዝ ስለሚቀለኝ ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ ልውሰዳችሁ፡፡

በእኔ እያቶች እድሜ ከሚስዮናዊያን ወንጌል አገልግሎት በኋላ በደቡብ ኢትዮጵያ አካባቢ ህበረተሰብ የነበረው የተለመደ ባህል፣ ቀስ በቀስ ሲለወጥ አብዛኛው በውዴታ የታጀበ አልነበረም፡፡ ከፊሎቹ ለወንጌል ከነበራቸው ጥማትና ከክርስቶስ ፍቅር የተነሳ ሁሉ ነገራቸውን ትተው ለመቀበል ፈቃደኛነታቸውን አሳይተዋል፡፡ ከባህል ጥያቄና "የነበረውና በፈረንጆቹ ባህል ያልተለመደው ሁሉ ተገቢ አይደለም" የሚለውን የሚሲዮናውያኑን ትርፍ ግዴታ ላለመቀበል የተሟገቱት ግን አልተቀላቀሉም፡፡ በአንድ ወቅት ላደረግሁት ጥናታዊ ጽሁፍ መረጃ ሳሰባስብ እንዳስተዋልኩት፣ አንዳንዱ አሰራር አሁን ያሉት የእምነቱ ተከታዮች እንኳ የማይደግፉት ነበር፡፡ ይህም ማለት የወንጌል መልእክቱ አቀራረብ የሰዎችን ቀዳሚ አኗኗርና ባህል በቅጡ ያላገናዘበና የሚስዮናውያኑ "ጫና" ያየለበት መሆኑን ነው፡፡ አንዳንዴም በሚሲዮናውያኑ ልማድ መስፈርት እየታየ



www.ethiocross.com

የነበረውን ባህል ሁሉ እስከማጥፋት "ጫናው" ከሚገባው በላይ በመክረሩ ባህሉን እንደጐዳው ብቻ ሳይሆን አገልግሎቱንም እንደጎዳው የሚተቹ የቤተ ክርስቲያን አባላትና ጽሁፋዊ መረጃዎች አሉ፡፡

ከጽሁፋዊ መረጃዎቹ ውስጥ፣ የኢትዮጵያ ቃለ ህይወት ቤተክርስቲያን "<u>በመከራ ውስጥ ያበበች ቤተ ክርስቲያን"</u> በሚል ርዕስ፣ በወንድዬ አሊ አማካኝነት ያዘጋጀችውን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ይህ የታሪክ መጽሐፍ የወቅቱን ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴና የባህል ለውጡን አስመልክቶ፣ አላስፈላጊ ግፊቶች እንደነበሩ ያረጋግጣል፡፡ ከተጻፈው ውስጥ የሚከተለውን ሀሳብ ለአስረጂነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ **"በሚሲዮናውያኑ ተጽእኖ ይመስላል፣ አልፎ አልፎ መጠን ያለፈና ሁኔታዎችን ያላገናዘበ እርምጃም ወስደዋል"**(1990፣ 161)፡፡ በተለይም አሁን ድረስ በአብዛኛው የሚዘወተረውን '**ጥሬ ስጋ መብላት**' የመሳሰሉትን ማውገዝ በወንጌል አማኞች ላይ ያስከተለው ችግር ከፍተኛ ነበር፡፡

ሌላው ግሬንስቴድ የተባለ ስዊዲናዊ የዶክትሬት ጥናቱን ባካሄደበት በደቡብ ኢትዮጵያ አካባቢ በሚሲዮናዊያኑ በተቋቋመው ቤተ ክርስቲያን ተንሠራፍቶ ስለነበረው አውሮፓዊ ባህልና አስተያየት አስመልክቶ **"የአውሮፖዊ ልማድና ደንብን የተከተሉ"** (2000፣108) በሚል የሚያነሳውን ሃሳብ፣ የኢትዮጵያ ቃለ ህይወት ቤተ ክርስቲያን ታሪክም በተዘዋዋሪ የሚደግፈው ይመስላል፡፡ በወቅቱ ክርስቲያን የነበሩት የመጡበትን ባህላዊ እምነት ልምምድና ተግባራት ባለመተዋቸው ፈረንጆች ያስተማሯቸውን ያጠናቀቁ ቢሆንም ጥምቀትን ለመፈጸም **"ፈተናውን ለማለፍ ያልበቁ ሆነው እንደተገኙ"** በተገለፀበት ስፍራ ከተጠቀሱት ውስጥ **"የበኣል ቀናት አቆጣጠር፣ በፈረንጅ ዘመን ያለመቁጠር ጉዳይ፣ ጥሬ ስጋ መብላት፣ ስር የሰደዱና አንዳንዶቹም ለማቋረጥ የሚከብዱና ሌላ ችግር የሚያስከትሉ"** እንደነበሩ በወቅቱ ሁኔታውን ያስተዋሉ እንደሚናገሩ ገልጾታል፡፡ በ"**አዎንታዊ ጎኑ**" ከሚጠቀሱት የሚሲዮናውያኑ አስተዋጽኦዎች መካከልም፦ **"ትንባሆ መጉረስ፣ ቦርዴ መጠጣት፣ ድርብ ጋብቻ፤ በቀብር ስነስርዓት ጊዜ ጠጉር መንጨት፣ ሰውነትን በስለት መቁረጥ፣ ጉንጭን በእሾህ መቧጠጥ፣ የሟቹን ንብረት ማውደምና መሰዋት፣ በተለያዩ ችግሮች የተነሣ ወደ ጠንቋይ ወይም ጠጠር ጣይ ወይም ኮከብ ቆጣሪ ዘንድ መሄድ፤ አማልክቱን ለመለማመን መስዋእት መሰዋት…"** የመሳሰሉትን ለማስቀረት ማገዛቸው በመጽሀፉ ሰፍሯል፡፡

ማህበረሰቡ ለረጅም ዘመናት ይዞት የቆየውን ልማድና መተዳደሪያ መንገድ ወዲያውኑ በራሳቸው ልማድና ሃይማኖት አረዳድ አንጻር ብቻ ለመተካት የሚያደርጉትን ጥረት አስመልክቶ፣ ሚስዮናዊያኑ "እሚወቀሱት" በዚያ በደቡብ ኢትዮጵያ አካባቢ ከደረሰባቸው መቋቋም አኳያ ብቻ አይደለም፡፡ በተለይም በአፍሪካና በቅኝ ግዛት በተያዙ ህዝቦች ላይ የደረሰው "ጫና" **(የዚህ ቃል አተረጓጎም እንደየዓላማው ሊለያይ ይችላል)** ተመሳሳይ ሁኔታ እንደተንፀባረቀበት፣ የፈረንጆቹም "የተሳሳተ አረዳድ" የሚደጋገም ስለመሆኑ የሚጠቁሙ ጥናቶች ብዙ አሉ፡፡ ለጊዜው ቀለል የሚለው ብርሃኑ ማቴዎስ (1986) የጻፈውን የኤም. ኤ. የእንግሊዝኛ ሥነ ጽሁፍ መመረቂያ ጽሁፍን ወይም አዪሲ (Ayisi) የተባለው ጋናዊ የጻፈውን ማንበቡ ነው (በዋቢ መጻህፍት ዝርዝር ውስጥ ያገኙታል)፡፡

በአንፃሩ ምክንያቶቹ በውል ባይረጋገጡም አልፎ አልፎ ከዚህ ከሚስዮናዊያኑ እሳቤ ጋር በሚጋጭ መልኩ ብቻ ሳይሆን፣ ሃይማኖቱን በራሳቸው ልማድና ባህል ውስጥ አስገብተው የመቀበልም ዝንባሌ ይታይ እንደነበር የሚያመለክቱ ሁኔታዎች አሉ፡፡ ለምሳሌ የመዝሙር ስልትን በተመለከተ **"የጋራ (የህብረት) ዝማሬዎች"** በማህበረሰቡ የተለመዱ የጭፈራና የተለያዩ ሀገረሰባዊ ዘፈኖችን (folk song) ስልት የተከተሉና በዚያው ዜማ ላይ የተመሰረቱ እንደነበሩ፣ አሁንም ድረስ በመጥፋት ላይ እያሉ እንኳ የሚታዩ



www.ethiocross.com

አሻራዎች አሉ፡፡ አለሙ ህምባሮ (በ1990 በግምት) በፃፈው መጽሐፍ **“የባህል መዝሙሮች ሲዘመሩ የነበረው ዜማ ቃና…ሰዎቹ ቀድሞ በሰይጣን ግዛት ውስጥ በነበሩበት ወቅት …ይጠቀሙበት የነበረውን የዜማ ቃና በቀጥታ ጌታን ወደ ማወደስ ለወጡት”** በማለት በቀደመው ልማድ የተቃኙ፣ ይዘታቸው ብቻ የተቀየረ ዜማዎች ምን ያህል ተወዳጅና ተዘውታሪ እንደነበሩ አስፍሯል፡፡

ይህ ግንዛቤ ዛሬ ሊሰራበት መጀመሩን በቅርቡ፣ **“በጥናት ላይ ተመስርቶ ቀርቧል”** በሚባለው የቤተልሄም ተዘራ ቁጥር 2 ቪሲዲ ካሴት ላይ በትክክል በመንጸባረቁ ከ70 ዓመታት በፊት ከነበረው ሁኔታ ጋር እየተነጻጸረ ነበር የታየኝ፡፡ በወቅቱ ‘በባህል ቀናኢነት’ ምክንያት የወንጌል ስርጭቱ ‘ሳንካ’ እንዲገጥመው ያደረገው ተግዳሮት ዛሬም መልኩን ቀይሮ እዚያው ሰፈር በበና አካባቢ አጋጥሞ እንደነበር ስሰማ፣ ምን ያህል ካለፈው ስህተት ለመማር የዘገየን እንደነበርን አስረድቶኛል፡፡ ከዚህ አኳያ የቪዲዮ ካሴቱ ይህንኑ መልእክቱን አቀነባብሮ፣ በተለያዩ ቋንቋዎችና ስልቶች ካካተታቸው ውብ መዝሙሮች ውስጥ የበናዎቹን ከነእነሱነታቸው መያዙን ስረዳ የአቀራረቡ ፍሬያማነት ነው ጎልቶ የታየኝ፡፡ በዚያው ቪሲዲ በደቡብ ኦሞ ለበናና ፀማይ ማህበረሰብ ወንጌልን የማድረስ እንቅስቃሴ የተጀመረው መቼ እንደነበረና ለምን ሳይሳካ እንደዘገየ የበናው ደሞ በዛብህ (የአሌባ ቃለ ህይወት ቤተ ክርስቲያን አባል) ራሱ እንዲህ ይነግረናል፡፡

> “መጀመሪያ ክርስትና ወደ እዛ ምድር ሲመጣ ይዘው የመጡት ወንጌላውያን ከሌላ አካባቢ ናቸው፡፡ ሲመጡ በራሳቸው አለባበስ ነው እዛ ያለውን ህብረተሰብ የቀረቡት፡፡ … ልብስ ለብሰው መጥተዋል፤ በራሳቸው አለባበስ ነው እዛ ያለውን ማህበረሰብ የቀረቡት፤ ወንዶች ሲመጡ ጸጉራቸውን ተቆርጠዋል፣ የበና ሴት ጸጉሯን በቀይ አፈርና በቅቤ ለውሳ ትሰራለች፤ ታዲያ ክርስቲያን የሆኑ ሰዎችን ‘ይህንን አታድርጉ’ ብለው ሲከለክሉ የባህል ሽግግር አድርገው ስለሚቆጥሩ አንድ ሰው ጌታን በመቀበሉ ባህሉን ሁሉ ለቅቆ እንደሚሄድ አድርጎ ያስባል፤ ከዚያ ጋር ተያይዞ ወደጌታ መምጣት ይከብድ ነበር፡፡ በና ሴት በራሷ አለባበስ ወደ እግዚአብሔር ቤት መጥታ በቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔርን ብታገለግል ምንም ችግር የለም፡፡
>
> የበና ወንድ እንዲሁ ሽርጥ ያገለድማል፤ ጨሌ በሰውነቱ ላይ አለ፤ አምባር ይኖራል፤ ያንን አድርጎ በጌታ ቤት ቢያገለግል ይህን ያህል ችግር የለም፡፡ ግን መጀመሪያ ወንጌል ይዘው የመጡ ሰዎች ያንን አስፈላጊ እንዳይደለ ሲናገሩ የተፈጠረው ምንድር ነው? - ልክ በና ክርስቲያን ሲሆን ባህሉን እንደሚተው በማሰብ ያመኑትን ሰዎች የሌላ ብሄረሰብ አባል አድርጎ የመውሰድና ባህልን የመቀየር አድርገው ስለሚወስዱት ብዙዎቹ ወደ ጌታ ቤት የሚመጡት ተስፋ ሲቆርጡ ነበር…

(“ጨለማችን በራ!” ተተሰኘውን የቤተ ልሄም ተዘራን መዝሙር መስማት ከፈለጉ የሚከተለውን መጫን ይችላሉ፡- http://www.youtube.com/watch?v=OKSmydr-hpQ )

ቀዳሚዎቹ አውሮፓውያን ሚስዮናውያን በራሳቸው ዘዬና ልማድ መሠረት አኮርዲዮናቸውን እየተጫወቱ ይዘምሩ በነበረበት ወቅት ቋንቋውንና ስልቱን ያልተረዳው ህዝብ ምላሽ የቀዘቀዘ እንደነበር ቀደም ሲል በጠቀስነው **“የቃለ ህይወቱ”** መጽሀፍ ተገልጿል፡፡ ቀስ በቀስ ህዝቡ የራሱን ባህላዊ ስልት የተከተሉ መዝሙሮችን መጠቀም ሲጀምር ተሳታፊነቱ እየጎላ እንደሄደና የራሱ እምነት እያደረገ እንደተቀበለው መረዳት ይቻላል፡፡ የሚሲዮናውያኑ ማበረታቻና መረዳት አላዋጣ ካለው ተጽእኖ ቀጥሎ ዘግይቶ ቢመጣም፣ በኢትዮጵያ ቃለ ህይወት ቤተ ክርስቲያን የታሪክ መጽሐፍ እንዲህ ተጠቅሷል፤ **“በደቡብ ኢትዮጵያ ከአውሮፓው ይልቅ የአገሬው አዘማመር ስልት አይሎ እንዲገኝ ምክንያት የሆነው፣ ይኸው የሚስዮናዊያኑ ማበረታቻ ሳይሆን አይቀርም”** (1990፣ 86):: እንደመጽሀፉ አቀራረብ **"ማበረታቻ"** የተባለው የሚስዮናውያኑን ተጽእኖ አለማየል ለማመልከት ይመስላል::

በተለይም አንዳንዶች እንደሚሉት ከመጽሀፍ ቅዱስ ከራሱ እየተጠቀሰ፣ ሰዎች እንዳይጠይቁና በፍርሃት ብቻ የተባሉትን እንዲያደርጉ ይገፋፉ ነበር፡፡ በተለይም፣ **“ወደ**



www.ethiocross.com

**እግዚአብሔር ቤት በገባህ ጊዜ እግርህን ጠብቅ፤ ለመስማት መቅረብ ከሰነፎች መስዋእት ይበልጣልና፣ እነርሱም ክፉ እንዲያደርጉ አያውቁምና እግዚአብሔር በሰማይ አንተም በምድር ነህና በአፍህ አትፍጠን፡፡ በእግዚአብሔር ፊት ቃል ይናገር ዘንድ ልብህ አይቸኩል፡፡ ስለዚህም ቃልህ ጥቂት ትሁን"** (መክብብ! 5!1-2) የሚለው ቃል ተደጋግሞ ይጠቀስ እንደነበር የሚያስታውሱ ሰዎች ባንድ ወቅት አጫውተውኛል፡፡ እስከሚገባኝ ድረስ የመክብቡ ጥቅስ በመጽሀፍ ቅዱሱ አውድ ከክርስትናው ጋር የማይጋፋውን ነባራዊውን ባህልና ልማድ ሁሉ ለማፋቻ ተብሎ እንዳልቀረበ ነው፡፡

ስለዚህ ወንጌል ወዳልደረሰበት አቅጣጫ በአካል ልንደርስ ስንነሳሳም ሆነ ሀሳቦቻችንን ስንልክ የማህበረሰቡን ባህልና የፎክሎሩን መሰረቶች ከጅምሩ መጋፋቱ ፍሬያማነታችንን እንደሚቀንሰው ማወቁ ተገቢ ነው፡፡ ከጸሎቱና ከቆራጥነቱ ባሻገር ከቸልተኝነትም ሆነ ካለመረዳት የተነሳ የሚከፈለው መስዋእትነት ያላስፈላጊ እንዳይሆን መጠንቀቅ ጠቃሚ ይሆናል፡፡ በዚህ መልኩ በአሁኑ ጊዜ **"ሀገር በቀል ሚሲዮናውያን"** ለሚያደርጉት እንቅስቃሴ እንደነዚህ ዓይነት ውይይቶችና የአሰራር ልምዶችን መጋራት የሚኖረው ረብ ከፍተኛ እንደሆነ አስባለሁ፡፡

**ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች፦** የተባለው የተሰባኪው ባህል ዕውቀት አናሳነትና እሱነቱን ያላገናዘበ የወንጌል መልእክተኝነት፣ ካልተመጣጠነና የወንጌል መልእክትነት አውዱ ሲዛባ የሚከተሉት ችግሮች ሊከሰቱ ይችላሉ፡፡

- የሚሰበክለት ወንጌሉን እንዳይቀበለው ምክንያት ይሆናል፤
- ወደ ክርስትና የሚመጡትንም ከማህበረሰቡ እንዲገለሉ ያደርጋቸዋል፤
- አገልጋዮች በባህል ላይ የዘመቱ ጠላቶች ተደርገው ሊቆጠሩና ለጥቃት ሊጋለጡ ይችላሉ፤
- ከባለ ባህሎቹ አንጻር ሲታይም "ማንነታቸውን የማጣት ነገር እንደገጠማቸው" (ወይም በዚያ ተጽዕኖ እንደደረሰባቸው) ክርስቲያንም ሆነው ሊሰማቸው ይችላል፤
- በቀናነት ሲታይ፣ ጎጂ እስካልሆነና በባለቤቶቹ ጠቃሚነቱ እስከተረጋገጠ ድረስ የነበረን ባህል እስከማጥፋት መዝለቁም ተገቢ አይሆንም፡፡

***ቀሪዎቹ ሁለት ርዕሶች እንደሁኔታው ቆየት ብዬ እመልስባቸዋለሁ፡፡ ከነዚህ አንደኛው፣ ለየት ያለ ሆኖ ያገኘሁትና "ቃለ መጠይቃዊ ዓይነት" ያልኩት የምስክርነትና ወንጌልን የማድረስ ዘይቤ ሲሆን ሌላው ወቅቱን ያስተዋሉና "ከጩሀት ያለፉ ዝማሬዎችን የወንጌል መልእክት" የሚመለከት ነው፡፡**

# ማጣቀሻዎች (RFERENCES)

**መጻህፍት**


አለሙ ህምባሮ (1990 ዓ.ም?) ፤ ወንጌል ነጻ ያወጣል፥ የወንጌል ስርጭት ታሪክ በከምባታና ሀዲያ። ኤስ.አይ.ኤም ማተሚያ ቤት፡፡

ወንድዬ ዓሊ (1990 ዓ.ም)፤ በመከራ ውስጥ ያበበች ቤተ ክርስቲያን፥ የኢትዮጲያ ቃለ ህይወት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፤ ቅጽ 1፤ አ. አ.፥ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

Ayisi, Eric O. (1979;Reprinted 1988). An Introduction to the study of African culture. Second Edition. London: Heinemann Educational




www.ethiocross.com

Books, Inc.
Brown, Ina Corinne (1963). Understanding other Cultures. Engle wood Cliffs, New Jersy: Printice-Hall, Inc.
Grenstedt, Staffan (2000). "Ambaricho and Shonkolla: Form local Independent Church to the Evangelical Main stream in Ethiopia. The origins of the Mekane Yesus church in Kembatta and Hadiya." Uppsala University: Faculty of Theology. Ph.D. dissertation. Sweden: Glanders Gotab, Stockholm.

## ኤሌክትሮኒክስ

ደሉ ጸጋዬ (2007)፤ "ከጥንት ግን እንዲህ አልነበረም" እና ሌሎች፡፡ የምስራች ድምጽ የመጻህፍትና የካሴት መሸጫ መደብር ያሳተማቸው መንፈሳዊ ቪሲዲዎች፡፡ አዲስ አበባ፤ ኢትዮጲያ፡፡
Bethelehem Tezera (2009). "Chelemacin Berra" — Gospel songs, VCD No.2. Resonance Production. Addis Ababa; Ethiopia.



www.ethiocross.com